***በሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት***
***Kinijit's Los Angeles Support and Development***
***Association for Democracy (KINIJIT)***
***5768 W. Pico Blvd., Suite No. 207, LA, CA 90019***
***E-mail*: kinijitla@kinijitla.org website www.kinijitla.org**

August 4, 2007

ይድረስ:

ኃላፊነታችሁን በአጥጋቢ መንገድ አከናውናችሁ አደራችሁን ከእስር ለተፈቱት መሪዎቻችን ለአስረከባችሁ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር አባላት

ለክቡር ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያም
ለክቡር አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ
ለክቡር አቶ ብርሃነ መዋ
ለክቡር ዶ/ር ገብርዬ ወልደ ሩፋኤል
ለክቡር አቶ ዳንኤል አሰፋ
ለክቡር አቶ ዳዊት ከበደ

በመጀመሪያ የአገራችን ነገር ያገባናል ብላችሁ በመነሳታችሁ፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ተሳትፎአችሁ ወደ ቅንጅት በመሸጋገር እውነተኛውን ውህደት የተቀበላችሁ፣ የአገር አለኝታነት እንጂ ወገናዊነት ለማይሰማችሁ የቅንጅትን ራዕይ ከግቡ ለማድረስ ቁርጠኝነታችሁን በሥራ ላስመሰከራችሁ አደራ ተቀባይ ብቻ ሳይሆን አደራንም አክባሪ ስለመሆነችሁ እጅግ በጣም እናከብራችኋለን::

ለአርቆ አሳቢነታችሁ፣ ለትእግሥታችሁ፣ ለታማኝነታችሁ፣ ለአስተዋይነታችሁ ለአስተማሪነታችሁ፣ ለፍቅራችሁ፣ ለወንድማማችነታችሁ፣ ለጊዜአችሁ፣ ለቆራጥነታችሁ፣ ለጽናታችሁ፣ ለተስፋ ሰጪነታችሁ፣ ለአሸናፊነታችሁ፣ ከሁሉም በላይ ለዲሞክራሲያዊነታችሁ፣ በሎስ አንጀለስና አካባቢው የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች አድናቆታችንን የምንገልጸው በእውነተኛው የቅንጅት መንፈስ እጅግ እየኮራንባችሁና እየተመካንባችሁ ነው:: ይልቁንም የተጣለባችሁን አደራ በምትወጡበት ወቅት በነገር ተገርፋችሁ፣ በሃሜት ተለብልባችሁ፣ እንቅልፍ በማጣት ተጎሳቁላችሁ፣ የግል ጥቅማችሁንና ኑሮአችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ኃላፊነቱን ስለተወጣችሁ አናደንቃችኋለን::

ብዙዎች ውድ ህይወታቸውን መስዋዕት የከፈሉበትን፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የነጻነት ታጋዮች ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ የተደበደቡበትንና በጣም አስቸጋሪና ብዙ አደጋ ባለበት ሁኔታ የተሰደዱበትን የቅንጅት ራዕይ ከግቡ ለማድረስ ከውድ መሪዎቻችን በአደራ የተሰጣችሁን ውክልና ተቀብላችሁ አቅማችሁ የሚፈቅደውን ሁሉ በማድረግ በየጊዜው ከአንዣበበበት አደጋ በመጠበቅ አደራ ለሰጡአችሁ መልሳችሁ ማስረከብ በመቻላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት ምስጋናችንን የምናቀርበው ከልብ በመነጨ ስሜት ነው::

***በሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት***
***Kinijit's Los Angeles Support and Development***
***Association for Democracy (KINIJIT)***
***5768 W. Pico Blvd., Suite No. 207, LA, CA 90019***
***E-mail*: kinijitla@kinijitla.org website www.kinijitla.org**

---

እኛ የሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድረጅት በችግር ተወልደን በእግራችን ቆመን መሄድ እስከጀመርንበት ድራስ ጉዞዋችን ብዙ ጠመዝማዛና ብዙ እንቅፋት በሞላበት መንገድ የነበረ በመሆኑ በአሳለፍነው ውጣ ውረድ እርዳታችሁን በፈለግንበት ግዚያቶች ሁሉ በአጭር ጊዜ ማሳሰቢያ ጥሪዎቻችንን በመቀበል በመካከላችን በመገኘት ከቅንጅት መርህ ሳንወጣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና፣ ዘመናዊ አሠራርን ከሁሉም በላይ ዲሞክራሲን ማዕከል ያደረገ አሠራርን ይዘን እንድንቀጥል ለአደረጋችሁት አስተዋጽዖ አሁንም ምስጋናችንን በድጋሜ እናቀርባለን::

በእሳት ተፈትናችሁ ያለፋችሁ፣ በትግሉ አመኔታ ያደረባችሁ የክፉ ቀን ደራሾች ናችሁና ፓርቲው በመደባችሁ ቦታ ሁሉ በብቃት ኃላፊነታችሁን የምትወጡ መሆናችሁን ምስክርነታችንን እየሰጠን ቅንጅት የቆመለትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ከማድረግ ወደኋላ እንደማትሉ ጽኑ እምነት አለን:: ወደፊትም በምትመደቡበት ቦታ ሁሉ እንዳለፈው ታጋሽነቱንና የመንፈስ ብርታቱን ይዛችሁ እንደትቀጥሉ የዘወትር ጸሎታችን ነው::

በሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት ለዲሞክራሲ